በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ተጠቃሚነት/ባለቤትነት ልዩነት በኢትዮጵያ፡

የሁለት ዓመት የጂ.ኤስ.ኤም.ኤ ሪፖርት ማጠቃለያ

TIKVAH MAGAZINE

ቲክቫህ መፅሄት

በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ተጠቃሚነት/ባለቤትነት ልዩነት በኢትዮጵያ



GSMA በዓለም ያሉ ከ 740 በላይ የሞባል ኦፕሬተሮችን እንዲሁም ከ400 በላይ ኩባንያዎችን ያቀፈ ተቋም ሲሆን ከሚያወጣቸው ሪፖርቶች መካከል በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ተጠቃሚነት/ባለቤትነት ልዩነት (The Mobile Gender Gap) ላይ የሚያተኩረው ሪፖርት ተጠቃሽ ነው። ተቋሙ ከ2017 ጀምሮ ይህንን ሪፖርት ማውጣት የጀመረ ሲሆን አትዮጵያን በ 2023 እንዲሁም በ 2024 ባወጣቸው ሪፖርቶቹ ውስጥ አካቷቷል።

ጥናቱ የተካሄደበት ስልት (Methodology)

- ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ የተካተተችበት ሪፖርት የወጣው በ2023 ሲሆን ለሪፖረቱ የሚሆን መረጃ የተሰበሰበው በ2022 ነው። በተመሳሳይ በ2024 የወጣው ሪፖርት ላይ የተካተተው መረጃ የተሰበሰበው በ2023 ነው።

- በሁለቱም ዙር የነበረው የመረጃ አሰባሰብ ገጽ ለገጽ በተደረገ ቃለመጠይቅ ሲሆን በዚህ ጥናት ላይ የተደረገው የተሳታፊ ብዛት (sample size) በሁለቱም ዶታ 1000 የሚደርሱ ሲሆኑ፤ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል በተለያዩ የኑሮ ዘይቤና የአኗኗር ሁኔታ ላይ ያሉ ኢትዮጵያዊያንን ያሳተፈ ነበር። ይህ የተሳታፊ የልየታ ሀገራዊ ውክልና እንዲኖረው ተደርጎ የተሰራ ሲሆን ጥናቱ በተደረገባቸው ሀገራት ላይ በሙሉ ወጥነት ያለው ነው።[1]

- በ2023 በወጣው ሪፖርት የትግራይ ክልል እና ሌሎች 6 ዞኖች በጸጥታ ምክንያት ማካተት ሳይቻል ቀርቷል።[2] ይህም 12 በመቶ የሆነውን የሀገሪቱን ክፍል የያዘ ነው። በተመሳሳይ በ2024 የወጣው ሪፖርት የአማራ ክልልን እና 4 ዞኖችን ማካተት ሳይችል ቀርቷል።[3] ይህም አጠቃላይ 27 በመቶ የሚሆነውን የሀገሪቱን ክፍል እንደሚይዝ ሪፖርቱ ጠቅሷል።

---

[1] በሪፖርቱ በተካተተችው ሀንድ የተሳታፊ ብዛት 2000 የሚጠጋ ተደርጎ ተወስዷል።

[2] መተከል ዞን (ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል)፤ ዞን ሁለት (አፋር ክልል)፤ ምዕራብ ወለጋ ዞን (ኦሮሚያ ክልል)፤ ጉጂ ዞን (ኦሮሚያ ክልል)፤ ቄለም ወለጋ ዞን (ኦሮሚያ ክልል) እና ሆሮ ጉዱሩ ዞን (ኦሮሚያ ክልል) ናቸው።

[3] ምዕራብ ትግራይ (ትግራይ ክልል)፤ መተከል ዞን (ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል) ዞን ሁለት (አፋር ክልል)፤ እና ጉጂ ዞን (ኦሮሚያ ክልል) ናቸው።

ፎርሙላ

$$\text{የወ.ሴ ስል.ተጠቃ/ባለቤ. ልዩ.} = \frac{(\text{የወ.ስል.ተጠቃ/ባለቤ. ልዩ.} - \text{የሴ.ስል.ተጠቃ/ባለቤ. ልዩ.})}{\text{የወ.ስል.ተጠቃ/ባለቤ. ልዩ.}} \times 100$$

የወ.ሴ ስል.ተጠቃ/ባለቤ. ልዩ. = በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ተጠቃሚነት/ባለቤትነት ልዩነት

የወ.ስል.ተጠቃ/ባለቤ. ልዩ. = የወንዶች የስልክ ተጠቃሚነት/ባለቤትነት

የሴ.ስል.ተጠቃ/ባለቤ. ልዩ. = የሴቶች የስልክ ተጠቃሚነት/ባለቤትነት

በጥናቱ የተሳተፉ ሀገሁት እነማን ናቸው?

2023



2024




የጥናቱ ግኝት

1. በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ባለቤትነት ልዩነት

ትርጉም

- የስልክ ባለቤትነት ማለት ማንኛውም ሰው ሲም የሚወስድ ወይም ሲም የማይቀበል ስልክ ኖሮት ቢያንስ በወር አንዴ ጥቅም ላይ የሚያውለው ሲሆን የስልክ ባለቤት ተብሎ በዚህ ጥናት ተቀምጧል።



በጥናቱ መሰረት በ2023 በኢትዮጵያ 75 በመቶ የሚሆኑት ወንዶች የስልክ ባለቤት ሲሆኑ የሞባይል ባለቤት የሆኑ ሴቶች ደግሞ 55 በመቶ ናቸው። በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው የስልክ ባለቤትነት ልዩነትም 27 በመቶ ነው። ይህ ቁጥር በ2024 በወጣው ሪፖርት ላይ ወንዶች 79 በመቶ ሴቶች ደግሞ 57 በመቶ ሆኖ የተቀመጠ ሲሆን ልዩነቱ 28 በመቶ ሆኗል።

በጥናቱ ከተሳተፉ ከሰሀራ በታች ካሉ ሀገራት በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው የስልክ ባለቤትነት ልዩነት በ2023 በኬንያ 6 በመቶ፤ በናይጄሪያ 5 በመቶ፤ እንዲሁም በሴኔጋል 13 በመቶ ነው። ኢትዮጵያ በጥናቱ ከተካተቱ 12 ሀገራት መካከል ከፓኪስታን (35 በመቶ ልዩነት ያስመዘገበች) ቀትሎ ከፍተኛ ልዩነት ያለባት ሀገር ሆና ትገኛለች። [4]

ለንጽጽር የቀረበ መረጃ

በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ባለቤትነት ልዩነት በዓለም አቀፍ ደረጃ የ2024 መረጃ



83%	የስልክ ባለቤት የሆኑ ሴቶች ቁጥር
8%	በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ባለቤትነት ልዩነት
405M	ምንም ስልክ የሌላቸው ሴቶች ቁጥር

በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ባለቤትነት ልዩነት ከሰሃሉ ብታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሩት ሀገሩት

[4] በ2024 በእነዚህ ሀገራት በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው የስልክ ባለቤትነት ልዩነት አላሳየም።

71%	የስልክ ባለቤት የሆኑ ሴቶች ቁጥር
13%	በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ባለቤትነት ልዩነት
95M	ምንም ስልክ የሌላቸው ሴቶች

የስልክ ባለቤት የሆኑ ሴቶች ቁጥር በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ባለቤትነት ልዩነት ምንም ስልክ የሌላቸው ሴቶች ቁጥር

2. በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ልዩነት

ትርጉም

በዚህ ጥናት የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚነት በዚህ ጥናት በተለያዩ ደረጃዎች ተቀምጠዋል። በዚህም፡-


- **የሞባይል ኢንተርኔት ተጠቃሚ ማለት፡-** በሦስት ወር አንዴ የስልክ ኢንተርኔት የሚጠቀም ማለት እንደሆነ ተቀምጧል።
- **ዕለታዊ የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚ ማለት፡-** በትንሹ በቀን አንድ ጊዜ በስልክ የኢንተርኔት አማራጭ አንድ አገልግሎት (ለምሳሌ፡- ሶሻል ሚዲያ፤ አላይን ስልክ መደወል ወ.ዘ.ተ) መጠቀም የሚል ትርጉም ተሰጥቶታል።
- **መደበኛ እና በርካታ አገልግሎቶችን በስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚ ማለት፡-** በቀን ውስጥ ቢያንስ ሦስት አገልግሎቶችን በስልክ ኢንተርኔት መጠቀም የሚችል በማለት ተገልጿል።

ምን ያህል ኢትዮጵያዊያን ስለ ስልክ ኢንተርኔት ግንዛቤ አላቸው?

		1 የስልክ ባለቤትነት	2 የሞባይል ኢንተርኔት ግንዛቤ	3 የሞባይል ኢንተርኔት ተጠቃሚነት	4 መደበኛ እና በርካታ አገልግሎቶችን በስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚ	
					መደበኛ የሞባይል ኢንተርኔት ተጠቃሚነት	በርካታ አገልግሎቶችን በስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚነት
2023	MEN	79%	64%	21%	11%	7%
	WOMEN	57%	52%	13%	7%	3%

		1 የስልክ ባለቤትነት	2 የሞባይል ኢንተርኔት ግንዛቤ	3 የሞባይል ኢንተርኔት ተጠቃሚነት	4 መደበኛ እና በርካታ አገልግሎቶችን በስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚ	
					መደበኛ የሞባይል ኢንተርኔት ተጠቃሚነት	በርካታ አገልግሎቶችን በስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚነት
2024	MEN	75%	62%	22%	14%	6%
	WOMEN	55%	47%	10%	6%	2%

ይህ ጥናት አንድ ሰው ከዚህ ቀደም የሞባይል ኢንተርኔት ተጠቅሞ ወይም የሞባይል ኢንተርኔት ባይጠቀምም እድሉ ቢኖረው መጠቀም መቻሉን ስለ ስልክ ኢንተርኔት ግንዛቤ አለው በማለት ያስቀምጣል። በዚህም በ2023 በወጣው ሪፖርት ኢትዮጵያ ስለ ስልክ ኢንተርኔት ግንዛቤ ያላቸው ወንዶች 62 በመቶ፤ ሴቶች ደግሞ 47 በመቶ መሆናቸውን ይጠቅሳል። በ2024 ይፋ በሆነው ሪፖርት ደግሞ ወንዶች 64 በመቶ ስለ ስልክ ኢንተርኔት እውቀት እንዳላቸው ያስቀመጠ ሲሆን ሴቶች በአንጻሩ 52 በመቶ ያህሉ ብቻ ስለ ስልክ ኢንተርኔት ግንዛቤ እንዳላቸው ገልጻል።



የ2023 ሪፖርት አዋቂ ከሚባሉት እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ ከሆነው አጠቃላይ የህዝብ ቁጥር በኢትዮጵያ የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚ ተብለው የተቀመጡት 22 በመቶ ወንዶች እንዲሁም 10 በመቶ ሴቶች ናቸው። የ 2024 ሪፖርት ደግሞ ወንዶች 21 በመቶ ተጠቃሚ ናቸው ሲል፤ ሴቶች በአንጻሩ13 በመቶ ተጠቃሚ መሆናቸው አስቀምጧል።


ዕለታዊ የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ቁጥር በ2024 ሪፖርት እንደተጠቀሰው ወንዶች 11 በመቶ እና ሴቶች ደግሞ 7 በመቶ እንደሆኑ ያስቀምጣል። መደበኛ እና በርካታ አገልግሎቶችን ይጠቀማሉ ብሎ ያስቀመጠው ደግሞ ወንድ 7 በመቶ ሴት 3 በመቶ የሚሆነውን ነው። ከላይ በተቀመጠው ፎርሙላ መሰረት በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚነት ልዩነት 57 በመቶ ይሆናል።

ይህንን ቁጥር በጥናቱ በ2024 ከተካተቱ ሌሎች ሀገራ ጋር ስናነጻጽረው ለአብነትም ኬኒያ ወንዶች 58 በመቶ የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚ ሲሆኑ ሴቶች ደግሞ 39 በመቶ ያህሉ ተጠቃሚ ናቸው። በናይጄሪያም ወንዶች 52 በመቶ የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚ ሲሆኑ ሴቶች በአንጻሩ 33 በመቶ ድርሻ አላቸው። በስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚነት በጥናቱ ከተሳተፉ 12 ሀገራት ኢትዮጵያ አነስተኛውን ቁጥር የያዘች ሲሆን ሁለተኛ አነስተኛ ቁጥር የያዘችው ኡጋንዳ 40 በመቶ ወንዶች እና 21 በመቶ ሴቶች የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚ መሆናቸውን ይገልጻል።

ምን ያህል ሰዎች ስልካቸው የኢንተርኔት ኔትዎርክ ማገናኘት እየቻለ ኢንተርኔት አይጠቀሙም?

ስልካቸው ከኢንተርኔት የሚገናኝ ሆኖ ኢንተርኔት የሚጠቀሙ እና የማይጠቀሙ

ከአጠቃላይ የህዝብ ቁጥር በመቶኛ (2024)



በ2024 በተቀመጠው መረጃ መሰረት በኢትዮጵያ ስልካቸው የኢንተርኔት ኔትዎርክ ማገናኘት እየቻለ እና ስለ ስልክ ኢንተርኔት መረጃው እያላቸው የማይጠቀሙ ሰዎች ወንዶች 43 በመቶ ሴቶች ደግሞ 39 በመቶ ይሆናሉ። ከዚህ በተጨማሪ ስልካቸው የኢንተርኔት ኔትዎርክ ማገናኘት እየቻለ እና ስለ ስልክ ኢንተርኔት መረጃው ሳይኖራቸው ቀርቶ የስልክ ኢንተርኔት የማይጠቀሙ ሰዎች ቁጥር በወንዶች 21 በመቶ በሴቶች ደግሞ 13 በመቶ እንደሚሆን ይጠቅሳል። ይህም በዚህ ዓመት በጥናቱ ከተሳፉት ሀገራት በሙሉ በቁጥር ከፍተኛው ነው።

ሐንጽጽር የቀረበ መረጃ

በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚነት ልዩነት በዓለም አቀፍ ደረጃ



66%	የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች ቁጥር
15%	በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚነት ልዩነት
785M	ኢንተርኔት የማይጠቀሙ ሴቶች

ከሰሃሉ በታች ባሉ ሀገሮት በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚነት ልዩነት



36%	የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚ የሆኑ ሴቶች ቁጥር
32%	በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ኢንተርኔት ተጠቃሚነት ልዩነት
200M	ኢንተርኔት የማይጠቀሙ ሴቶች

ኢትዮጵያዊያን ምን አይነት የተንቀሳቃሽ ስልክ ይጠቀማሉ




ትርጉም

- **መደበኛ የእጅ ስልክ (በተለምዶ ኤርጌንዶ የሚባሉት)፡-** ምንም ዓይነት የስልክ ኢንተርኔት የማይቀበል፤ ስልክ ለመደወልና ለማንሳት እንዲሁም አጭር የስልክ መልዕክት ለመላላክ የሚጠቅም፤
- **መለስተኛ ስልክ (Feature phone)፡-** በተወሰነ መልኩ የኢንተርኔት ማሰሻ (Internet Browser) ያለው፤ አነስተኛ መተግበሪያዎን ማውረድ የሚችሉ፤
- **ስማርት ስልኮች፡-** ሙሉ ለሙሉ የስልክ ኢንተርኔት መጠቀም የሚያስችሉ

ጠቅላላ የህዝብ ብዛት በተንቀሳቃሽ ስልክ አይነት

ከአጠቃላይ የህዝብ ቁጥር በመቶኛ



በ2024 የGSMA ሪፖርት መሰረት እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ ከሆኑት ኢትዮጵያዊያን ወንዶች 34 በመቶ እንዲሁም ሴቶች 25 በመቶ የሚሆኑት በተለምዶ መደበኛ የእጅ ስልክ(በተለምዶ ኤርጌንዶ የሚባሉትን) የሚይዙ ሲሆን 20 በመቶ ወንዶች እና 10 በመቶ ሴቶች መለስተኛ ስልክ (Feature phone) ይጠቀማሉ። በኢትዮጵያ የስማርት ስልክ ተጠቃሚዎች ከ18 ዓመት በላይ ከሆኑ ወንዶች 20 በመቶው ሴቶች ደግሞ 15 በመቶው ብቻ ናቸው።

በጥናቱ ከተካተቱ 12 ሀገራት ኢትዮጵያ አነስተኛ የስማርት ስልክ ተጠቃሚ ያላት ሀገር ናት። ለአብነትም በኬንያ ወንዶች 52 በመቶ፤ ሴቶች ደግሞ 37 በመቶ የስማርት ስልክ ተጠቃሚዎች ናቸው። በናይጄሪያም ወንዶች 51 በመቶ፤ ሴቶች ደግሞ 32 በመቶ የስማርት ስልክ ተጠቃሚዎች ናቸው። ከኢትዮጵያ በመቀጠል አነስተኛ የስማርት ስልክ ተጠቃሚዎች ያላት ኡጋንዳ ወንዶች 29 በመቶ፤ ሴቶች ደግሞ 20 በመቶ የስማርት ስልክ ተጠቃሚዎች ናቸው።

እንደ ተግሮት የተነሱ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ስለ ስልክ ኢንተርኔት እውቀቱ ኖሯቸው ነገር ግን ለመጠቀም ተግዳሮት የሆኑ ነገሮች በጥናቱ ተካተዋል። በዚህም፦

ወንዶች የሚጠቅሱት ተግዳሮት በቅደም ተከተል

1. በኢትዮጵያ ወንዶች የአቀም እጦት
2. የዲጂታል እውቀት ክፍተት እና
3. ያስፈልገኛል ብሎ አለማሰብ

ሴቶች የሚጠቅሱት ተግዳሮት በቅደም ተከተል

1. የአቅም እጦት
2. የአቀም እጦት
3. ያስፈልገኛል ብሎ አለማሰብ

ሴቶች ከወንዶች በተሸለ መልኩ የስልክ ኢንተርኔት የመጠቀም ፍላጎት እንዳላቸውም ጥናቱ ያነሳል።

በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለ የስልክ ተጠቃሚነት/ ባለቤትነት ልዩነት በኢትዮጵያ፡

የሁለት ዓመት የጂ.ኤስ.ኤም.ኤ ሪፓርት ማጠቃለያ

CONTACT

+251 91 313 4524

Info@tikvahethiopia.net

Tikvahethiopia.net

ቲክቫህ መፅሄት

TIKVAH MAGAZINE